# SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

# የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

# SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

4ki Diro Kiiro ….

Hawaasa, Sadaasa 17/2016 M.D

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaale Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

፬ኛ ዓመት ቁጥር ….

ሀዋሳ፣ ታህሳስ ፲፯/፳፻፲፮ ዓ.ም



**<u>Amado</u>**

**Wodhote Kiiro 33/2016**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Dubbu, Qarqaru Agarooshshinna Diilallote Gade Soorro Biilloonyi Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodho …… Qoola ….**

**<u>ማውጫ</u>**

**ደንብ ቁጥር ፴፫/፳፻፲፮**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የደን፣ የአከባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ ባለሥልጣንን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ……. ገጽ ….**


## Wodhote Kiiro 33/2016

## Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Dubbu, Qarqaru Agarooshshinna Diilallote Gade Soorro Biilloonyi Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodho

Qarqaru diilaallote iibbilli lexxo dandaate babbaxxitino irkote wolqa horonsi'ra, iibbille kalaqqanno gaazete lexxo ajisha, moolanna du'namanno ishinenna daaffanno kemikaalla ajishatenna karboonete latishshanna horonsi'rate amanyoote diriirsatenni mootimmanna dagoomu

## ደንብ ቁጥር ፴፫/፳፻፲፮

## የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የደን፣ የአከባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ ባለሥልጣንን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ

የአከባቢ አየር ሙቀት መጨመርን ለመቋቋም የተለያዩ ታዳሽ የኃይል አማራጮችን መጠቀም፣ ሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠን መቀነስ፣ የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ እና በካይ ኬሚካሎችን መቀነስ እና የካርቦን ምርትና አጠቃቀም ሥርዓትን በመዘርጋት መንግሥትና ኅብረተሰብን ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል አስፈላጊ

horaameeyye ikkitanno gede assa hasiissannota ikkasenni;

Kalqoomuamuraatenna baci-lubbote jiro aana gawajjo iillitannokki gede agarooshshe assa, lubbo noonsarinna noonsakki bissa kalaqamu irkisamansa danni soorramikkinni seeda yanna sufisa, ajate woy ba”ate huluullo xaaddinore batinyi-lubbote jiro agaranna dubbu jilba ledatenni moolle gargara qara hajo ikkasenni;

Kalaqamunna mannu loosino dubbu latishshanna xiinxallo assatenni, doogimale dubbu haqqe tareessa gargaratenninna qorqorushu hayyo kaajjishatenni, dagoomu beeqqonna miinja lossatenni mootimmanna dagooma horaameeyye assa hasiissannota ikkitinohura;

Qoqqowu giddo heedhanno dubbu saada jironna galtinonsa qarqarira hala’lanni daynoha ajatena ba”ate qarri jifo uurrisatenna jawa dubbu saada gumma doogimale tareessanna daddala qorqoratenninna massagatenni jiro qarqaru agarooshshira, miinju lophoranna daa”atote latishshira hattono xiinxallotenna buuxxo assate hosiisatenni mootimmanna dagooma horaameeyye assa qara haja ikkasenni, hattono hegeraamo latishsha darga gananno assa hasiisannoha ikke leellinohura;

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma jeefisiisaanote amaale mini qooqqowu mootimma jeefisiisaano bissa uurrisate, biilloonyenna loosu qeecha murate fulino laallawa kiiro 3/2012 quwa 10 cinaancho quwa 12 iima uynoonisi biilloonyi kaiminni tenne wodho fushshino.

በመሆኑ፣

በሥርዓተ-ምህዳር እና ብዝሀ-ሕይወት ሀብት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ጥበቃ ማድረግ፣ ሕይወት ያላቸውና የሌላቸው አካላት የተፈጥሮ መስተጋብር ሳይዛባ በዘላቂነት ማስቀጠል፣ የመመናመን ወይም የመጥፋት ስጋት የተጋረጠበትን የብዝሀ-ሕይወት ሀብት መጠበቅ እና የደን ሽፋን በመጨመር በረሀማነትን መከላከል ወሳኝ በመሆኑ፣

የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ደን ልማትና ምርምር በማካሄድ፣ ሕገ-ወጥ የደን ውጤቶች ዝውውርን በመከላከልና የጥበቃ ሥርዓቱን በማጠናከር፣ የኅብረተሰቡን ተሳትፎና ኢኮኖሚውን በማሳደግ መንግሥትና ኅብረተሰብን ተጠቃሚ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፣

በክልሉ በሚገኘው የዱር እንስሳት ሀብትና መኖሪያ አካባቢያቸው እየተባባሰ የመጣውን የመመናመንና የሕልውና ፈተናን መግታትና ከፍተኛ የዱር ሕይወት ውጤቶች ሕገ-ወጥ ዝውውርና ንግድን በመቆጣጠርና በመምራት ሀብቱ ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለኢኮኖሚ ዕድገትና ለቱሪዝም ልማት እንደዚሁም ለጥናትና ምርምር በማዋል መንግሥትንና ኅብረተሰብን ተጠቃሚ ማድረግ ወሳኝ በመሆኑ፣ እንዲሁም ዘላቂ ልማትን ማሳካት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት የክልሉን አስፈፃሚ አካላት ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፫/፳፻፲፪ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ ፲፪ ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## GAFA MITE

## Xaphooma Woro

**1. Ha’rancho Umo**

Tenne wodho “Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Dubbu, Qarqaru Agarooshshinna Diilallote Gade Soorro Biilloonyi Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodho Kiiro 33/2016 yine woshshinara dandiinanni.

**2. Tiro**

Qaalu horo wole tiro uytannota ikka hoogguro tenne wodho giddo:

1. **"Qoqqowo"** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti.
2. **"Biloonye"** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Qarqaru, Dubbunna Diilallote Gade Soorro Qorqorshi Biloonye yaate.
3. **"Qara Dayrekitere"** yaa Biilloonyu qara dayrekitereeti.
4. **“Layinki Dayrekitere”** yaa biilloonyu layinki dayrekitereeti.
5. **"Qarqara"** yaa baattotenni, qarqaru diilallonni, diilallote suudinna diilallote gadenni, waay giddo heedhannorinni, huurotenni, su’niillunni, coommillunni, dagoomu hajubbanna biinfillunni bandikkinni kalaqamu suudinsanni woy mannunni woyyaabbeenna soorrante leeltannore wo’mankanna noo darga hattono bikkansa woy danansa woy mannu woy wolou kalaqamiha dancha ikkito kissanno xaadooshshinsa xaphishshaati.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የደን፣ የአከባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ ባለሥልጣንን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፴፫/፳፻፲፮ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. **“ክልል”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው::
2. **"ባለሥልጣን"** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአካባቢ ጥበቃ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ባለሥልጣን ነው።
3. **"ዋና ዳይሬክተር"** ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ነው።
4. **"ምክትል ዳይሬክተር"** ማለት የባለሥልጣኑ ምክትል ዳይሬክተር ነው።
5. **"አካባቢ"** ማለት በመሬት፣ በከባቢ አየር፣ በአየር ሁኔታና በአየር ንብረት፣ በውሃ ህያዋን፣ በድምፅ፣ በሽታ፣ በጣዕም፣ በማህበራዊ ጉዳዮችና በሥነ-ውበት ሳይወሰን በተፈጥሯዊ ሁኔታቸው ወይም በሰው አማካይነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉና ያሉበት ቦታ እንዲሁም መጠናቸውን ወይም ሁኔታቸውን ወይም የሰው ወይም የሌሎች ህያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ መስተጋብሮቻቸው ድምር ነው::

6. **"Moola Ishine"** yaa dihasi’nanniho yine hunnoonniha ayee du’namannonna du’namannokkirichooti.
7. **"Daafama"** yaa tenne wodhonni woy hasiisanno wolu seerinni xawinsoonnire ayee gadacho, roqqo woy gawalo sae ayee qarqara caange, iibbille, kalaqamu heeshsho woy wole akata soorratenni kalanqoonniha, mannu keeranchimma woy danchumma woy wolootu heeshsho aana busha ikkinoha woy busha ikkara dandaanno garaati;
8. **"Diilallote Gade Soorro"** yaa ajanni ajeenna 30 diro istatistikete mereerima diilallote gade akataati;
9. **"Diilallote Gade Soorro Rosama"** yaa kalaqamunni woy manchu beetti iillishanno hekkonni iillitara danidiitanno haaro woy soorrantanno diilallote gade soorro gawajjo ajisha woy ikkitote ledo taashshate.
10. **"Diilallote Gade Soorro Diwo"** yaa qarqara gawajjitanno gaazubba fooraro ajishatenna gargarate.
11. **"Dubbu"** yaa dubbu baattora, dooggate qaccera, laggate qaccera, irshunna saadate hayisso kallanni baatto giddonna qoxeessira hattonno gallanni minna qoxeesiranna paarkete giddo kalaqamunni mudhinota woy kaanseenna woy wole doogonni lattino haqqenna mu’ro hattonno wolootu baci-lubbote kuusooti.

6. **"ደረቅ ቆሻሻ"** ማለት የማይፈለግ ተብሎ የተጣለ ማንኛውም ፈሳሽ ወይም ፈሳሽ ያልሆነ ነገር ነው፡፡
7. **"ብክለት"** ማለት በዚህ ደንብ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ህግ የተደነገገን ማንኛውንም ግዴታ፣ ማዕቀብ፣ ወይም ገደብ ጥሶ የማንኛውም የአካባቢ ክፍል፣ ቁሳዊ፣ ጨረራዊ፣ ሙቀታዊ፣ ነገራዊ፣ ሥነ ሕይወታዊ ወይም ሌላ ባህሪይን በመለወጥ የተፈጠረ፣ በሰው ጤና ወይም በጎነት ወይም ደግሞ በሌሎች ህያዋን ላይ አደገኛ የሆነ ወይም አደገኛ ሊሆን የሚችል ሁኔታ ነው፡፡
8. **"አየር ንብረት ለውጥ"** ማለት ቢያንስ የ30 ዓመታት ስታትስቲካዊ አማካይ የአየር ንብረት ፀባይ ነው፤
9. **"የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣም"** ማለት በተፈጥሮ ወይም በሰው ልጅ ተፅዕኖ ሊደርስ የሚችልን አዲስ ወይም ተለዋዋጭ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳት መቀነስ ወይም ከሁኔታዎች ጋር ማስተካከል ነው፡፡
10. **"የአየር ንብረት ለውጥ ስሪየት"** ማለት አካባቢን የሚበክሉ ጋዞችን ልቀት መቀነስ ወይም መከላከል ነው፡፡
11. **"ደን"** ማለት በደን መሬት፣ በመንገዶች ዳርቻ፣ በወንዝ ዳርቻ፣ በእርሻና በግጦሽ መሬቶች ውስጥና በዙሪያቸው እንዲሁም በመኖሪያ አካባቢዎችና ፓርኮች ውስጥ በተፈጥሮ የበቀሉ ወይም ተተክለው ወይም በሌላ ዘዴ የለሙ የዛፎችና የእጽዋት እንዲሁም ሌሎች የብዝሀ-ህይወት ክምችት ነው፡፡
12. **"የደን ውጤት"** ማለት ማንኛውም ከደን

12. **"Dubbu Guma"** yaa ayereno dubbunni afi'nanni haqqu dani noosinna noosikki laalchi, hattono dubbu karbooneno lede ayehano dubbu kalqoomuamuraati horo amadannoho.
13. **"Dubbu Kaarboone Daddalo"** yaa dubbu buujjamanna anje ajishatenni woy dubbu amado lossatenninna karboonete kuuso ledatenni karboonete fooraro ajishate batooshshe assinanni dikki'rate amanyooteeti.
14. **"Baci-Lubbo"** yaa aye kalqoomuamuraatira heedhanno lubbo noonsari mereero leellanno babbadooshshe ikkanna, kunino sirchu giddo, sirchunna kalqoomuamuraati mereero noo babbadooshsheno amaddannoho.
15. **"Kalqoomuamuraate"** yaa lubbo noonsa kalaqami lubbo noonsakkiri ledo mittimmate heedhanno qarqara woy baychooti.
16. **"Noowa Heedheenna Agara"** yaa siddo woy baci-lubbote jiro kalaqamunni afantanno base giddo heedhanno ikkitooti.
17. **"Basete Gobbaanni Agara"** yaa siddo woy baci-lubbote jiro kalaqamunni afantanno qarqari woy kalqoomuamuraati gobbaanni heedhanno ikkitooti.
18. **"Wodani Gede Afamate"** yaa siddote woy baci-lubbote jiro kalaqamunni afantanno base gobbaanni woy dagoomu

የሚገኝ የእንጨትነት ባህሪይ ያለውና የሌለው ምርት እንዲሁም የደን ካርቦንን ጨምሮ ማንኛውንም የደን ሥርዓተ-ምህዳራዊ ግልጋሎት የሚያካትት ነው፡፡

13. **"የደን ካርበን ንግድ"** ማለት የደን ምንጣሮንና መመናመንን በመቀነስ ወይም የደን ሽፋንን በማሳደግና የካርቦን ክምችትን በመጨመር ለካርቦን ልቀት ቅነሳ ክፍያ የሚፈጸምበት የግብይት ሥርዓት ነው፡፡
14. **"ብዝሀ-ሕይወት"** ማለት በየትኛውም ስርዓተ-ምህዳር የሚገኙ ሕይወት ባላቸው ነገሮች መካከል የሚገኙ ተለያይነት ሲሆን ይህም በዝርያዎች ውስጥ፣ በዝርያዎች እና በሥርዓተ-ምህዳሮች መካከል ያለውን ተለያይነት ይጨምራል፡፡
15. **"ሥርዓተ-ምህዳር"** ማለት ሕይወት ያላቸው ፍጥረታት ሕይወት ከሌላቸው ጋር በመስተጋብር የሚኖሩበት አካባቢ ወይም ስፍራ ነው፡፡
16. **"ዘ-ቦታ ጥበቃ"** ማለት የጄኔቲክ ወይም የብዝሀ-ሕይወት ሀብት በተፈጥሮ ከሚገኝበት ቦታ ውስጥ የሚገኝበት ሁኔታ ነው፡፡
17. **"ኢዘ-ቦታ ጥበቃ"** ማለት የጄኔቲክ ወይም የብዝሀ-ሕይወት ሀብት በተፈጥሮ ከሚገኝበት አከባቢ ወይም ስርዓተ ምህዳሩ ውጭ የሚገኝበት ሁኔታ ነው፡፡
18. **"አርክቦት"** ማለት የጄኔቲክ ወይም የብዝሀ-ሕይወት ሀብት በተፈጥሮ ከሚገኝበት ቦታ ውጭ ወይም የማህበረሰብ ዕውቀትን

egenno gamba assate, adhate, saysate woy horonsi’rate.

19. **"Gobbaydinni Dayno Horri Sirchi"** yaa kalaqamu qarqari woy kalqoomuamuraati gobbaanni leellatenni jawu garinni bati’ratenni woy wolu korkaatinni wolootu baci-lubbote jiro heeshshora yaaddo ikkitanno mu’ro woy saadaati.

20. **"Dubbu Saada"** yaa mini saada agurranna lubbote nooha woy reynoha badhete miqqichi noonsarinna noonsakki sadaati.

21. **"Dubbu Saada Agarranni Base"** yaa danna baxxite afantino goboomu parke, seeru garinni saada ugaanxanni base, dubbu saada galtannowa, dubbu saada agarranni base, dagoomu gashshanno dubbu saada agarranni base, shiimmaada paarkuwa, saada ce’nanniwanna hossannowaati.

22. **"Dubbu Heeshsho"** yaa danna bande anfoonnita gobba saada agarooshshi base giddoonnino ikko gobba saada agarooshshi gobbaanni afantanno mu’ronna gobba saada sirchooti.

23. **"Gobba Saada Guma"** yaa ayee gobba saada, gobba saadanni afi’nanniricho, quuphe, ice, zibaade, buuda, hinko, culunqa, goga, maala, danancho, farro, baallicho, gofilanna ceate mineeti.

24. **"Konseeshini"** yaa mitte mootimmate baattora seeru garinni ugaaxete looso

መሰብሰብ፣ መውሰድ፣ ማስተላለፍ ወይም መጠቀም ነው፡፡

19. **"መጤ ወራሪ ዝርያ"** ማለት ከተፈጥሮ አካባቢው ወይም ስርዓተ-ምህዳር ውጭ በመገኘት በከፍተኛ ሁኔታ በመራባት ወይም በሌላ ምክንያት ለሌሎች ብዝሀ-ሕይወት ሀብቶች ህልውና አስጊ የሚሆን እፅዋት ወይም እንስሳት ማለት ነው፡፡

20. **"የዱር እንስሳት"** ማለት ከቤት እንስሳት በስተቀር በሕይወት ያለ ወይም የሞተ የጀርባ አጥንት ያለው ወይም የሌለው እንስሳ ነው፡፡

21. **"የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ"** ማለት ወሰኑ ተለይቶ የታወቀ ብሔራዊ ፓርክ፣ ሕጋዊ የአደን ቦታ፣ የዱር እንስሳት መጠለያ፣ የዱር እንስሳት ጥብቅ ቦታ፣ በማኅበረሰብ የሚተዳደር የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ፣ ራንች፣ እርባታ እና መዋዕለ-እንስሳት ነው፡፡

22. **"የዱር ሕይወት"** ማለት ወሰኑ ተለይቶ በታወቀ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ ውስጥም ሆነ ከዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ ውጭ የሚገኝ ዕፅዋትና የዱር እንስሳት ዝርያ ነው፡፡

23. **"የዱር እንስሳት ውጤት"** ማለት ማንኛውም የዱር እንስሳ፣ ከዱር እንስሳ የተገኘ አካል፣ እንቁላል፣ እጭ፣ ዝባድ፣ ቀንድ፣ ጥርስ፣ ጥፍር፣ ቆዳ፣ ሥጋ፣ ፀጉር፣ ጭራ፣ ላባ፣ ጎፍላና የወፍ ጎጆ ነው፡፡

24. **"ኮንሴሽን"** ማለት አንድን የመንግስት መሬት ሕጋዊ የአደን ሥራ ለማካሄድ ለተወሰነ ጊዜ

loosate bikkinoonni yannara seeru mannimma noosi bisira sheemaatunni sayse aate.

25. Tenne wodjo giddo mitte koo-teemmanni xawinsoonnihu wole koo-teemmano kamalanno.

**GAFA LAME**

**<u>Biilloonyu Biilloonyenna Loosu Qeecha</u>**

**3. Qara Borro Mine**

Biilloonyunihu qaru borrote mine Hawaasi quchumira ikkanno. Hasiishshu garinni wole dargano tantano heedhasira dandiitanno.

**4. Hexxo**

Biilloonyu hexxo ajjanni noota baci-lubbonnita kalaqamu jiro agaratenninna iillanni nooha qarqaru dafama ajishatenni faayya, co’ichanna heeshshote injaano qarqara kalaqatenni dubbu latishshanna agarooshshe woyyeessatenni dubbu jironni afi’nanni ikonoomete, dagoomunna kalaqoomuamuraate kaa’lo lossa, baci-lubbote jiro garunni horonsi’nannita, horote aana hossannotanna fitihaawe jirote horo beeqqaanchimma hala’litanno gede assatenni hegeraamo latishsha kalaqate.

**5. Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Biilloonyeho konni woroonni noo biilloonyinna

ሕጋዊ ሰውነት ላለው አካል በውል ማስተላለፍ ነው፡፡

**25. በዚህ ደንብ ውሥጥ በአንድ ፆታ የተገለፀው ሌላውንም ፆታ ያካትታል፡፡**

**ክፍል ሁለት**

**<u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>**

**3. ዋና መሥሪያ ቤት**

የባለሥልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት በሀዋሳ ከተማ ይሆናል፡፡ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎችም መዋቅር ሊኖረው ይችላል፡፡

**4. ዓላማ**

የባለስልጣኑ ዓላማ በመመናመን ላይ የሚገኙ የብዝሀ-ህይወት የተፈጥሮ ሀብቶችን በመጠበቅና እየደረሰ ያለውን የአካባቢ ብክለት በመቀነስ ውብ፣ ፅዱና ለኑሮ ምቹ አካባቢ መፍጠር፣ የደን ልማትና ጥበቃ በማሻሻል ከደን ሀብት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ስነ-ምህዳራዊ አስተዋፅኦ ማሳደግ፣ የብዝሀ-ሕይወት ሀብት በአግባቡ የሚጠቀምበት፣ ጥቅም ላይ የሚውልበትና ፍትሀዊ የሀብት፣ የጥቅም ተጋሪነት እንዲሰፍን በማድረግ ዘላቂ ልማትን ማሳካት ነው፡፡

**5. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር

loosu qeechi hee’rannosi:

1. Mootimmateno ikko hallanyu pirojekitwaa, mittimmatenna miinju latishshi seerinna jeefishshu mixubba aana qarqaru gawajjo qorqorsha assate dandiisissanno hayyo diriirsanno; loosu aana hosiisanno.
2. Wolootu bissanni buuxante shiqqannosi qarqaru gawajjo odoo keenanno; fajjo uytanno bissara gumulo egenisiissanno; loosu aana hosasi harunsanno; qorqorsha assanno; hasiissanno qaafo adhanno.
3. Qoqqowu gashshooti giddo ayeno uduunne loosanno woy owaante uytanno uurrinshuwa qarqaru gawajjo gargaratenna dubbo agarate gadacho agarisiisate fulino seera agadhite millisansa buuxanno; qorqorsha assanno; hasiissanno qaafo adhanno.
4. Co’ichanna haanja qarqara kalaqate moolanna du’namanno ishini amadooshshinna hunate hayyo amanyooti hee’ranno assanno; huurote daafama qorqorsha assanno; qaafo adhanno; adhinanni gede assanno; ishine wirro hige horote aana hosiisa dandiisissanno tekinolooje injonna bu’a badanno; haja la’anonsa bissa ledo qinaawe loosu aana hosano gede assanno.
5. Gawajjannoricho woy cingoo qixxeessa, tareessa, amadooshshe, hunnanni garanna horonsi’nanni hayyo hattono qarqaru deerra lainohunni fultino polisubbanna seerubba loosu aana hosansa harunsanno; qorqoranno.

ይኖሩታል፡-

1. በመንግሥትም ሆነ በግል ፕሮጀክቶች፣ በማህበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ የልማት ህጎች እና መርሃ-ግብሮች ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፡፡
2. በሌላ አካል ተጠንቶ የሚቀርብለትን የአካባቢ ተፅዕኖ ዘገባ ይገመግማል፣ ለፈቃድ ሰጪው አካል ውሳኔውን ያሳውቃል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡
3. በክልሉ ስልጣን ወሰን ውስጥ ማናቸውም የማምረቻ ወይም የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት አካባቢውን ከብክለት ለመከላከልና የደን ጥበቃ ግዴታዎች ለማስጠበቅ የወጣውን ሕግ ጠብቀው መንቀሳቀሳቸውን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡
4. ፅዱ እና አረንጓዴ አከባቢን ለመፍጠር የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤ የድምፅ ብክለት ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤ ያስወስዳል፤ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ መዋል የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ አማራጮችን እና ምንጮችን ይለያል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
5. አደገኛ ነገሮችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ማዘዋወርን፣ አያያዝ፣

6. Hegeraamo qarqaru amadooshshe guutisate dandiisissannota qarqara xawissanno mashalaqqe gamba assate; tantanatenna horonsi'rate amanyoote kalaqanno; qinaawa qarqaru garanna soorrote odoo qixxeessanno; loosu aana hosanno gede assanno.
7. Diilallote gade soorro hekko uurrisate dandiisissanno rosamatenna diwote jeefishshi-mixo qixxeesanno; massaganno; iibbillu bu'a ikkitino gaaze bikkantanno gede assanno.
8. Halallimma gargaratenna moolle gantino kalqoomuamuraate wirro gatamarantanno hayyo burqisanno; loosu aana hosase harunsanno.
9. Dubbu xiinxallonaa latishsha halashshate dandiisissanno gibaate batishsha, dubbu mu'ro wixa isilanchimma qorqorshu uurrinshshanna labiratoore uurrissanno; gashshanno.
10. Kalaqamunna mannu loosino dubbi latishshi, agarooshshenna horonsi'rate amanyoote kalaqanno; latissanno; latanno gede assanno; gawajjamatenni agaramanno gede assanno; laalcho aanno dubbo horonsi'rate gara gumulanno.
11. Qoqqowu dubbu jiro mashalaqqe soorri'rate amanyoote kalaqatenni qoqqowunniha dubbu mashalaqqe horaameeyyete iillannoha assanno.
12. Dubbo latissannori eggennonna dandoo lophitanno gede ogimmate irko aanno.

አወጋገድና አጠቃቀም እንደዚሁም የአካባቢ ደረጃዎችን አስመልክቶ የወጡ ፖሊሲዎችን እና ሕጎችን ተፈፃሚነታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡፡

6. ዘላቂ የአካባቢ አያያዝ ለማስፈን የሚያስችል የአካባቢ አመላካቾች መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፣ የተቀናጀ የአካባቢ ሁኔታ እና የለውጥ ዘገባ ያዘጋጃል፤ እንዲተገበር ያደርጋል፡፡

7. የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ለመቋቋም የሚያስችል የማጣጣሚያ እና የስሪየት መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል፣ ሙቀት አማቂ ጋዞች እንዲለኩ ያደርጋል፡፡
8. በረሃማነትን ለመከላከል እና የተራቆተ ሥርዓተ-ምህዳር መልሶ ማገገም የሚያስችል ስልት ይቀይሳል፣አተገባበሩን ይከታተላል፡፡
9. የደን ምርምር እና ልማት ለማስፋፋት የሚያስችሉ የግብዓት ማባዣ፣ የደን ዕፅዋት ዘር ጥራት ቁጥጥር ማዕከላትና ላብራቶሪዎችን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፡፡
10. የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያለማል፣ እንዲለማ ያደርጋል፤ ከጉዳት እንዲጠበቅ ያደርጋል፤ የምርት ሰጪ ደኖች አጠቃቀም ይወስናል፡፡
11. በክልሉ የደን ሀብት መረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመዘርጋት የክልሉን ደን መረጃ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ያደርጋል፡፡

12. የደን አልሚዎች ዕውቀትና ክህሎት እንዲያድግ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

13. Qoqqowu shiimmaaddanna manaadda, mereerimanna jawa dubbu indusitirra hala’litannonna heewisamaanno ikkitanno gede irko assanno.
14. Dubbu gumi deerri fulanno gede assanno.
15. Hegeraamonna yannillicho dubbu latishshi agarooshshenna horonsi’rate amanyoote kalaqatenni woriidi tantanora tekiniketenna uduunnu irko assanno.
16. Dubbu latishshi agarooshshe, horonsi’rate ekisiteenshiinenna dikko halashshate loosi amanyoote kalaqanno.
17. Dubbu gumi aana horote beeqqoshshe gumulate dandiisisanno amanyoote kalaqanno.
18. Qoqqowu giddo heedhannota ayeno dubbu baattonna mootimmate dubbo gashshanno; hallanshu, maamarunnihanna dagoomu dubbo Itiyophiyu federaalete dimokiraasete ripublike (IFDR) dubbu latishshi, agarooshshinna horonsi’rate lallawi kiiro 1065/2010 kaiminni latansanna agaramansa qorqoranno; irkisanno; hasiise leelliro qaafo adhanno.
19. Qoqqowoho dubbunna dubbu baatto seeru afamooshshe afidhanno gede assanno.
20. Qoqqowoho dagooma beeqqaancho assinoha dubbu latishshi pirograame hala’litanno gede jawaachishanno; ogimmate irkono aanno.
21. Dubbu baattora baattote amadooshshe horonsi’rate fajjo uynoonnihu ayeno dubbu

13. በክልሉ ጥቃቅንና አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ የደን ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ድጋፍ ያደርጋል፡፡
14. የደን ውጤት ደረጃዎች እንዲወጣ ያደርጋል፤
15. ዘላቂ እና ዘመናዊ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ሥርዓት በመዘርጋት ለታችኞቹ መዋቅሮች የቴክኒክና የማቴሪያል ድጋፍ ያደርጋል፡፡
16. የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ኤክስቴንሽንና ገበያ ማስፋፋት ሥራዎች ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
17. በደን ውጤቶች ላይ የጥቅም ተካፋይነትን ለመወሰን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
18. በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውንም የደን መሬት እና የመንግሥት ደን ያስተዳድራል፤ የግል፣ የማህበራት እና የማህበረሰብ ደኖች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዲሪ) የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1065/2010 መሠረት መልማታቸውን፣ መጠበቃቸውንና እና መተዳደራቸውን ይቆጣጠራል፣ ይደግፋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እርምጃ ይወሰዳል፡፡
19. በክልሉ ደንና የደን መሬቶችን ሕጋዊ ዕውቅና እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
20. በክልሉ ሕብረተሰቡን ያሳተፈ የደን ልማት ፕሮግራም እንዲስፋፋ ያበረታታል የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፡፡
21. ለደን መሬት በመሬት ይዞታ የመጠቀም መብት የተሰጣቸው ማንኛውም ደን አልሚ

latisaanchi, baatto dubbu latishshi hexxo garinni hosassenna qixxaabbanno dubbu amadooshshi mixo garinni loosamase yanna yannate harunsonna keeno assanno.

22. Qoqqowu giddo dubbu jiro aana horritanno fayya kalaqantanokki gedenna dubbu giira ka’annokki gede gargaranno; kalaqanturono rahotenni uurritanno gede assanno.
23. Dubbu latishshinna gumma horonsi’ratenna tareessate fajjo aanno; qorqorsha assanno, qaafo adhanno; qaafo adhinanni gede assanno.
24. Dubbu ogimma, dubbu latishshinna dubbu gumma daddali dandoote xawishshi fajjo aanno.
25. Qoqqowu giddo dubbu gumma royaalitete bikka qoqqowu mootimmara shiqishe gumulisiissanno; gambano assanno.
26. Dubbu jiro aana gawajjo iillitannokki gede balaxote qorophishsha, gargarooshshenna qorqorate amanyoote qixxeessanno; gawajjo kalaqanturono dagoomanna woloota hajo la’annonsa bissa qineessatenni rahote qaafo adhanno; hasiisanno garinni federaalete bissa irko xa’manno.
27. Dagate beeqqonni laayyo kaima assino dubbu latishshi loossara annu hee’rannonsa gede assanno.
28. Dubbu xiinxallo, rosunna qajeelshu uurrinshubba, mootimmannita ikkitinnokki uurrinshanna hajo la’anonsa bissa ledo baadillichonna yannillitte dubbu amadooshshi egenno lophitanno gede waaxotenninna halamatenni loossanno amanyoote kalaqanno.
29. Haqqa ikkitinokki dubbu gumma latishshi agarooshenna horonsi’rate amanyoote

መሬቱን ለደን ልማት ዓላማ ማዋሉንና በሚዘጋጀው የደን አያያዝ ዕቅድ መሠረት መተግበሩን በየጊዜው ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፡፡

22. በክልሉ ውስጥ በደን ሀብት ላይ ወረርሽን እንዳይከሰትና የደን ቃጠሎ እንዳይነሳ ይከላከላል፣ ከተከሰተም በአፋጣኝ በቁጥጥር ስር እንዲውል ይደረጋል፡፡
23. ለደን ልማትና ውጤቶች አጠቃቀምና ዝውውር ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፡፡
24. የደን ሙያ፣ የደን ልማትና የደን ውጤቶች የንግድ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
25. በክልሉ ውስጥ የደን ውጤቶች ሮያሊቲ ተመን ለክልሉ መንግሥት አቅርቦ ያስወስናል፣ ይሰበስባል፡፡
26. በደን ሀብት ላይ አደጋ እንዳይከሰት የቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ የመከላከያ እና የመቆጣጠሪያ ሥረዓት ያዘጋጃል፤ አደጋ ሲከሰትም ህብረተሰቡንና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር አፋጣኝ እርምጃ ይወስዳል፤ እንደስፈላጊነቱ የፌዴራል አካላትን ድጋፍ ይጠይቃል፡፡
27. በኅብረተሰብ ተሳትፎ ተፋሰስን መሰረት ያደረጉ የደን ልማት ስራዎች ባለቤት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡
28. የደን ምርምር፣ ትምህርትና የስልጠና ተቋማት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር ሀገር በቀል እና ዘመናዊ የደን ዕውቀቶች እንዲያድጉ በቅንጅትና በትብብር የሚሰሩበትን ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
29. እንጨት ያልሆኑ የደን ውጤቶች ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፣

kalaqanno; jiro lattannonna agarantanno gede assanno.

30. Dubbu karboone hirantanno invesitimentete mixo qixxeessanno; loosu aana hossanno gede assatenni dagoomu horo afi'ranno gede assanno.
31. Qoqqowu giddo afantannota bayo-sifere agaranno; gashshanno; wolootu hajo la'annonsa bissa ledo qinaawe ledote bayo-sifere xiinxallantanno, huxxantannonna kalqete deerrinni borreessanteenna gashshootu amanyooti hee'rannonsa gede assanno.
32. Qoqqowu gido ba''ate huluullo xaaddino baci-lubbo jiro basete hedheennanna basete gobbaanni agarantanno gede assanno.
33. Baci-lubbote jiro kassenyinna horo beeqqate amanyoote kalaqanno; fajjo aanno; loosu aana hosase harunsanno; qorqorsha assano; qaafo adhanno; qaafo adhinanni gede assanno.
34. Gobbaydinni dayno horanno sirchi tuqannotanna hala'lannota qorqoranno; dagoomunna hajo la'annonsa mootimmannitanna mootimmaamme ikkitinnokki bissa qineessatenni ba'anno gede assanno.
35. Kalqoomuamuraati horo waagi birrunni bikkamanno gede assanno; loosu aana hossiisanno; horameeyyimma buuxanno.
36. Qoqqowu goboomu parke gobbaanni heedhano dubbu saadanna dubbu saada agarooshi base agaranno; latisanno;

ሀብቶቹ እንዲለሙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡

30. የደን ካርቦን ሽያጭ ኢንቨስትመንት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ ኅብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
31. በክልሉ የሚገኙ ባዮ-ስፌሮችን ይጠብቃል፣ ያስተዳድራል፣ ከሌሎች አካላት ጋር በመቀናጀት ተጨማሪ ባዮስፌሮች እንዲጠኑ፣ እንዲከለሉና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመዝግቦ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲዘረጋላቸው ያደርጋል፡፡
32. በክልሉ የመጥፋት ስጋት የተጋረጠበትን የብዝሀ-ሕይወት ሀብት በዘ-ቦታና በኢዘ-ቦታ እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡
33. የብዝሀ-ሕይወት ሀብት አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ሥርዓት ይዘረጋል፤ ፍቃድ ይሰጣል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡
34. የመጤ ወራሪ ዝርያዎች ስርጭትና መስፋፋትን ይቆጣጠራል፣ ሕብረተሰቡን እና የሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን በማስተባበር እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡
35. የሥርዓተ-ምህዳር ግልጋሎት ዋጋ በገንዘብ እንዲተመን ያደርጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ተጠቃሚነትን ያረጋግጣል፡፡
36. በክልሉ ከብሔራዊ ፓርክ ውጭ የሚገኙ የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ይጠብቃል፤ ያለማል፤ ያጠናል፤

xiinxallanno; danna huxxanno; deerrase gumulanno; seerunni borreesantanno gede assanno; hasiissanota ikkitino hajo aana la’annonsa bissa ledo qinaawe loosanno; irkisanno.

37. Goboomu parke gobbaanni heedhanno dubbu saada afantanno base woy dubbu saada agarantanno base dagoomunni, hallanyunni woy mootimmannita ikkitinnokki dirijjitta uurratenna tantanamate dandiitanno hayyo burqisanno; fajjo aano; hasiissanno irkonna qorqorsha assanno.

38. Dubbu saadanna insawiinni afi’nanni guma seerimale daddalanna basetenni base tareessa qorqoranno, mittu qoqqowinni wolu qoqqowira woy qoqqowu giddo tareesate dandiisissanno fajjo aanno; loosu aana hosase harunsanno; qorqoranno; wolu bisira sa’anno woy horote gobbaanni ikkitanno gede assanno; seeru qaafo adhanno; adhisiisanno.

39. Hexxosi jeefisiissate kaa’litanno woloota labbanno loossa loosanno.

## GAFA SASE

## BIILLOONYU TANTANONNA GASHSHOOTE

### 6. Tantano

Biilloonyeho aante noo tantano heedhanosi:

1. Qoqqowu pirezidaantichinni somamanno

ወሰን ይከልላል፤ ደረጃ ይወስናል፤ ህጋዊ ዕውቅናም እንዲያገኙ ያደርጋል፤አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋርም ተቀናጅቶ ይሰራል፣ይደግፋል።

37. ከብሔራዊ ፓርክ ውጭ የሚገኙትን የዱር እንስሳት መገኛ ቦታዎች ወይም የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በማህበረሰብ፣ በግል ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች መቋቋምና መደራጀት የሚችሉበትን ስልት ይነድፋል፣ ፈቃድ ይሰጣል፤ አስፈላጊውን ድጋፍና ቁጥጥር ያደርጋል።

38. የዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ሕገ-ወጥ ንግድና ዝውውርን ይቆጣጠራል፤ ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው ክልል ወይም በክልሉ ውስጥ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣል፤ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ለሌላ አካል እንዲተላለፍ ወይም እንዲወገድ ያደርጋል፤ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ ያስወስዳል።

39. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

## ክፍል ሦስት

## <u>የባለሥልጣኑ አደረጃጀት እና አስተዳደር</u>

### 6. አደረጃጀት

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት አደረጃጀቶች ይኖሩታል፡-

1. በርዕሰ መስተዳድር የሚሾም ዋና

qaru dayirekiterichinna layinki dayirekiterichi,

2. Dayrekitoreetete deerrinni gaamantanno loosu sooreeyyenna wolootu hasiissanno loosaasine heedhanosi.

**7. Qaru Dayrekiterichi Biilloonyenna Loosu Qeecha**

1. Tenne wodho quwa 5 hunda worroonni biilloonyenna loosu qeecha jeefisanno.
2. Biilloonyunnita istirateejikenna diru mixo, loosu pirogiraamenna bajeete qixxeesse la’’annonsa bissara shiqishanno; fajjiniro loosu aana hosiisanno.
3. Biilloonyeho fajjinoonni bajeetenna loosu pirogiraame kaiminni loosiissanno.
4. Sayikki wogane ledo assinanni xadooshshira biilloonye lekkisanno.
5. Biilloonyunnita jeefishshu rippoorte la”annonsa bissara shiqishanno.

**8. Layinki Dayrekiterichi Biilloonyenna Looso Qeecha**

1. Qaru dayrekiterichi hee’rannokki yannara riqiwe loossanno.
2. Rosamino garinni mitte biilloonyu tantano massaganno.
3. Qaru dayrekiterichinni bande uyiinanni loossa loosanno.

ዳይሬክተርና ምክትል ዳይሬክተር፣

2. በዳይሬክቶሬት ደረጃ የሚመደቡ የሥራ ኃላፊዎች እና ሌሎች አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

**7. የዋና ዳይሬክተር ስልጣንና ተግባር**

1. በዚህ ደንቡ አንቀጽ 5 የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፡፡
2. የባለሥልጣኑን ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
3. ለባለሥልጣኑ በተፈቀደ በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ያሰራል፡፡
4. ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ባለሥልጣኑን ይወክላል፡፡
5. የባለሥልጣኑን የአፈፃፀም ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፡፡

**8. የምክትል ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር**

1. ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡
2. በመደበኛነት አንድ የባለሥልጣኑን አደረጃጀት ይመራል፡፡
3. በዋና ዳይሬክተሩ ተለይቶ የሚሰጡ ተግባራት ያከናውናል፡፡

## GAFA SHOOLE

## Addi Addi Woro

**9. Baajetete Bu’a**

Biilloonyu baajete konni woroonni noo bu’anni ikkitanno:

1. Qoqqowu mootimmanni gaamantanno baajeete,
2. Qixeessanno laalchininna aano owaantenni gamaba assinanni eonna
3. Kaa’lo assitanonna bissawininna woloototu bu’anni.

**10. Shallaggote Taje**

1. Biilloonyu wo’manna guuta ikkitinota shallaggote taje amadanno;
2. Biilloonyu shallaggonna woxu ledo xaaddanno taje qoqqowu qara odiiterenni woy insanni riqiwantino wole odiiterenni buuxantanno.

**11. Reekkote yanna wodho**

Konni albanni hanafantinonna tenne whodhonni kamalantino hajubba lainohunni tini wodho loosu aana hossanno.

**12. Jeefishshu Nookki Seerinna Assooti**

Tenne wodho ledo kiphi yaannohu aye seeri woy rosamino assooti tenne wodhonni hanqafantino hajubbara jeefishshu diheeranosi.

**13. Biddissa Fushshate Biilloonye**

Tenne wodho loosu aana hosiisate hasiissanno biddissuwa piresidantichu borro mini fushshate dandaanno.

**14. Wodho Loosu Iima Hossanno Yanna**

Tini wodho Sadaasa 17/2016 M.D hanafe loosu aana hossanno.

Hawaasa, Sadaasa 17/2016 M.D

**Desta Ledamo**
**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaanticha**

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**9. የበጀት ምንጭ**

የባለሥልጣኑ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች ይሆናሉ፡-

1. የክልሉ መንግስት ከሚመድበው በጀት፣
2. ከሚያመርታቸው ምርቶች እና ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚሰበሰብ ገቢ እና
3. ከድጋፍ ሰጪ አካላትና ከሌሎች ምንጮች፡፡

**10. የሒሳብ መዛግብት**

1. ባለሥልጣኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል፤
2. የባለሥልጣኑ ሒሳብና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር ወይም በእርሱ በሚሰየም ሌላ ኦዲተር ይመረመራል፡፡

**11. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ከዚህ በፊት የተጀመሩና በዚህ ደንብ ውስጥ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ይህ ደንብ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**12. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕግና አሰራር**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**13. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ይህንን ደንብ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን የርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ሊያወጣ ይችላል፡፡

**14. ደንቡ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከታህሳስ ፲፯ ቀን ፳፻፲፮ ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

ሀዋሳ፣ታህሳስ ፲፯ ፳፻፲፮ ዓ.ም

**ደስታ ሌዳሞ**
**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት**
**ርዕሰ መስተዳድር**